የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራአምስተኛ ዓመት ቁጥር ፶፯
አዲስ አበባ ነሐሴ ፳፪ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

15th Year No. 57
ADDIS ABABA 28th August, 2009

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፮፻፶፪/፪ሺ፩ ዓ.ም

የፀረ ሽብርተኝነት አዋጅ… ገጽ ፬ሺ፰፻፳፯

CONTENTS

**Proclamation No. 652/2009**

Anti-Terrorism Proclamation …..Page 4827

## አዋጅ ቁጥር ፮፻፶፪/፪ሺ፩

## ስለፀረ ሽብርተኝነት የወጣ አዋጅ

ሕዝቦች በሰላም፣ በነጻነትና በተረጋጋ ሁኔታ ለመኖር ያላቸው መብት ከሽብርተኝነት አደጋ ሁል ጊዜ መጠበቅ ያለበት በመሆኑ፤

ሽብርተኝነት ለሀገራችን ሰላም፣ ደኅንነትና ዕድገት ፀር እንደሆነ፣ ለአካባቢያችንና ለዓለም ሰላም እና ደህንነትም ከፍተኛ ስጋት እንደሆነ ግንዛቤ የተወሰደ በመሆኑ፤

በስራ ላይ ያሉት የሀገሪቱ ሕጎች በበቂ ሁኔታ ሽብርተኝነትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችሉ ባለመሆናቸው ጠንካራ የሕግ አቅም መፍጠር በማስፈለጉ፤

ሽብርተኝነትን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠርና ለማ-ምከን በቂ መረጃዎችንና ማስረጃዎችን ለማሰባሰብና ለማጠናቀር፣ በሽብርተኝነት የተጠረጠሩ ሰዎችን ወይም ድርጅቶችን ለሕግ ለማቅረብ የሚያስችሉ የተጠናከሩ የምርመራና ክስ የማቅረብ አዳዲስ ስልቶችንና ስርዓቶችን በሕግ ማቋቋም አስፈላጊ በመሆኑ፤

ሽብርተኝነትን በሚገባ ለመዋጋት የፀረ-ሽብርተ-ኝነት ዓላማ ካላቸው የአካባቢያችን፣ የአሕጉራችንና የሌላው የዓለም ክፍሎች መንግስታትና ሕዝቦች ጋር መተባበር እና በተለይ ከተባበሩት መንግስታትና ከአፍሪካ ሕብረት አባል ሀገራት ጋር የተደረጉትን ስምምነቶች ስራ ላይ ማዋል አስፈላጊነቱ የታመነበት በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## PROCLAMATION NO. 652/2009

## A PROCLAMATION ON ANTI-TERRORISM

**WHEREAS**, the right of the people to live in peace, freedom and security has to be protected, at all times, from the threat of terrorism;

**WHEREAS**, terrorism is a danger to the peace, security and development of the country and a serious threat to the peace and security of the world at large;

**WHEREAS**, it has become necessary to legislate adequate legal provisions since the laws presently in force in the country are not sufficient to prevent and control terrorism;

**WHEREAS**, it has become necessary to incorporate new legal mechanisms and procedures to prevent, control and foil terrorism, to gather and compile sufficient information and evidences in order to bring to justice suspected individuals and organizations for acts of terrorism by setting up enhanced investigation and prosecution systems;

**WHEREAS**, in order to adequately fight terrorism, it is necessary to cooperate with governments and peoples of our region, continent and other parts of the world that have anti-terrorism objectives and particularly, to enforce agreements that have been entered into under the United Nations and the African Union;

**NOW, THEREFORE**, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የፀረ ሽብርተኝነት አዋጅ ቁጥር ፮፻፶፪/፪ሺ፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩/ "ንብረት" ማለት ማናቸውም ግዙፍነት ያለው ወይም የሌለው ወይም ተንቀሳቃሽ ወይም የማይንቀሳቀስ ሀብት ሲሆን፣ የባንክ ሂሳብን የመሰሉ የዚሁ ንብረት ወይም ሀብት ባለሃብ ትነትን ወይም ጥቅምን የሚያስረዱ ሰነዶችና ደብተሮችን ያካትታል፤

፪/ "ከሽብርተኝነት ድርጊት የተገኘ ንብረት" ማለት ገንዘብን ጨምሮ በማንም ስም፣ ይዞታ ወይም ቁጥጥር ስር ቢገኝም ከሽብርተኝነት ድርጊት በመነጨ ንብረት አማካኝነት የተገኘ ወይም የተፈራ ማናቸውም ንብረት ነው፤

፫/ "የሽብርተኛ ንብረት" ማለት ከሽብርተኝነት ድር-ጊት የተገኘ ንብረት፣ የሽብርተኛ ድርጅት ንብረት ወይም የሽብርተኝነት ድርጊት ለመፈፀም የዋለ፣ እየዋለ ያለ ወይም የሚውል ንብረት ነው፤

፬/ "ሽብርተኛ ድርጅት" ማለት፡-

ሀ) የሽብርተኝነት ድርጊትን የመፈፀም ዓላማ ያለው ወይም የሽብርተኝነት ድርጊት ለመፈፀም ያቀደ፣ የተዘጋጀ፣ የፈፀመ፣ ያስፈጸመ ወይም እንዲፈፀም በማናቸውም ሁኔታ የረዳ ወይም ያነሳሳ ከሁለት ያላነሱ አባላትን የያዘ ቡድን፣ ማህበር ወይም ድርጅት፣ ወይም

ለ) በዚህ አዋጅ መሰረት በሽብርተኝነት የተሰየመ ድርጅት፣

ነው፤

፭/ "እገታ ወይም ጠለፋ" ማለት ሰውን በመያዝ ወይም በቁጥጥር ስር በማድረግ የያዘውን ሰው ለመልቀቅ መንግስት አንድ ነገር ካላደረገ የያዘውን ሰው እንደሚገድል፣ ከባድ ጉዳት እንደሚያደርስበት ወይም እንደማይለቀው መዛት ነው፤

፮/ "ማነሳሳት" ማለት ድርጊቱ ባይሞከርም ሌላውን ሰው በመጎትጎት፣ ተስፋ በመስጠት፣ በገንዘብ፣ በስጦታ፣ በማስፈራራት ወይም በማናቸውም ሌላ ዘዴ የሽብርተኝነት ድርጊት እንዲፈጸም ማግባባት ነው፤

፯/ "የህዝብ አገልግሎት" ማለት ለህዝብ አገል-ግሎት ለመስጠት የተደራጁ የኤሌክትሮኒክ፣ የኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን፣ የትራንስፖርት፣ የፋይናንስ፣ የህዝብ ግልጋሎት መስጫ፣ የመ ሰረተ ልማት ወይም እነዚህን የመሰሉ ተቋማት ወይም ስርአቶች ነው፤

## PART ONE
## GENERAL

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Anti-Terrorism Proclamation No.652/2009".

### 2. Definitions

In this Proclamation, unless the context otherwise requires:

1/ "property" means any asset whether corporeal or incorporeal or movable or immovable, and includes deeds and instruments evidencing title to or interest in such asset such as bank accounts;

2/ "proceeds of terrorism" means any property, including cash, derived or obtained from property traceable to a terrorist act, irrespective of a person in whose name such proceeds are standing or in whose possession or control they are found;

3/ "terrorist property" means proceeds of terrorism, properties of a terrorist organization or property which has been or is being or will be used to commit a terrorist act;

4/ "terrorist organization" means:

a) a group, association or organization which is composed of not less than two members with the objective of committing acts of terrorism or plans, prepares, executes or cause the execution of acts of terrorism or assists or incites others in any way to commit acts of terrorism; or

b) an organization so proscribed as terrorist in accordance with this Proclamation;

5/ "hostage taking or kidnapping" means seizing or detaining and threatening to kill, to injure or to continue to detain a person in order to compel the government to do something as a condition for the release of the hostage;

6/ "incitement" means to induce another person by persuasion, promises, money, gifts, threats or otherwise to commit an act of terrorism even if the incited offence is not attempted;

7/ "public services" means electronic, information communication, transport, finance, public utility, infrastructure or other similar institutions or systems established to give public service;

፰/ "ዲጂታል ማስረጃ" ማለት በዲጂታል ቅርፅ የተቀመጠ ወይም የተላለፈ የማስረጃነት ዋጋ ያለው ሆኖ በማናቸውም ማስተላለፊያ ላይ በኮምፒውተር፣ በኮምፒውተር ውስጥ ወይም በሌላ ተመሳሳይ መሳሪያ የተቀረፀ ወይም የተቀመጠ በሰው፣ በኮምፒውተር ወይም በተመሳሳይ መሳሪያ መነበብ ወይም መረዳት የሚችል መረጃ ሲሆን በመግለጫ፣ በህትመት ወይም በሌላ መንገድ የሚወጣ የዚህኑ መረጃ ውጤት ይጨምራል፤

፱/ "መንግስት" ማለት የፌዴራል መንግስት ወይም የክልል መንግስት ወይም የመንግስት አካል ወይም የውጭ ሀገር መንግስት ወይም የዓለም አቀፍ ድርጅት ነው፤

፲/ "ፍርድ ቤት" ማለት እንደ አግባብነቱ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወይም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ነው፤

፲፩/ "ፖሊስ" ማለት የፌዴራል ፖሊስ ወይም የፌዴራል ፖሊስ ሥልጣን በውክልና የተሰጠው የክልል ፖሊስ ማለት ነው፤

፲፪/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፲፫/ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል::

## ክፍል ሁለት

## ስለሽብርተኝነት እና ተያያዥ ወንጀሎች

### ፫. የሽብርተኝነት ድርጊቶች

ማንኛውም ሰው ወይም ቡድን የፖለቲካ፣ የሃይማኖ-ታዊ ወይም የአይዲዮሎጂ ዓላማን ለማራመድ በማሰብ በመንግሥት ላይ ተፅዕኖ ለማሳደር፣ ህብረተሰቡን ወይም የህብረተሰቡን ክፍል ለማስፈራራት ወይም የሃገሪቱን መሠረታዊ ፖለቲካዊ፣ ህገመንግሥታዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ወይም ማህበራዊ ተቋማትን ለማናጋት ወይም ለማፍረስ፡-

፩/ ሰውን የገደለ ወይም በአካሉ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ፤

፪/ የህብረተሰቡን ወይም የህብረተሰቡን ክፍል ደህንነት ወይም ጤና ለከፍተኛ አደጋ ያጋለጠ እንደሆነ፤

፫/ እገታ ወይም ጠለፋ የፈፀመ እንደሆነ፤

፬/ በንብረት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ፤

8/ "digital evidence" means information of probative value stored or transmitted in digital form that is any data, which is recorded or preserved on any medium in or by a computer system or other similar device, that can be read or perceived by a person or a computer system or other similar device, and includes a display, printout or other output of such data;

9/ "government" means the federal or a state government or a government body or a foreign government or an international organization;

10/ "court" means Federal High Court or Federal Supreme Court, as the case may be;

11/ "police" means Federal Police or Regional State Police to whom the power of the Federal Police is delegated;

12/ "person" means a physical or juridical person;

13/ any expression in the masculine gender includes the feminine.

## PART TWO

## TERRORISM AND RELATED CRIMES

### 3. Terrorist Acts

Whosoever or a group intending to advance a political, religious or ideological cause by coercing the government, intimidating the public or section of the public, or destabilizing or destroying the fundamental political, constitutional or, economic or social institutions of the country:

1/ causes a person's death or serious bodily injury;

2/ creates serious risk to the safety or health of the public or section of the public;

3/ commits kidnapping or hostage taking;

4/ causes serious damage to property;

፭/ በተፈጥሮ ሀብት፣ በአካባቢ፣ በታሪካዊ ወይም የባህል ቅርስ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ፤

፮/ ማናቸውንም የህዝብ አገልግሎት ለከፍተኛ አደጋ ያጋለጠ፣ የያዘ፣ በቁጥጥር ስር ያደረገ፣ ያቋረጠ ወይም ያበላሸ እንደሆነ፤ ወይም

፯/ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (፩) እስከ (፮) ከተመለከቱት ድርጊቶች መካከል ማናቸውንም ለመፈጸም የዛተ እንደሆነ፤

ከ፲፭ አመት እስከ እድሜ ልክ በሚደርስ ጽኑ እስራት ወይም በሞት ይቀጣል፡፡

## ፬. የሽብርተኝነት ድርጊት ለመፈፀም ማቀድ፣ መዘጋጀት፣ ማሴር፣ ማነሳሳትና ሙከራ

ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፫ ከንዑስ አንቀጽ (፩) እስከ (፮) የተመለከተውን ማናቸውንም የሽብርተኝነት ድርጊት ለመፈፀም ያቀደ፣ የተዘጋጀ፣ ያሴረ፣ ያነሳሳ ወይም የሞከረ እንደሆነ በዚሁ አንቀጽ በተቀመጠው መሠረት ይቀጣል፡፡

## ፭. ለሽብርተኝነት ድጋፍ መስጠት

፩/ ማንኛውም ሰው የሽብርተኝነት ድርጊት አፈፃፀምን ወይም የሽብርተኛ ድርጅትን የሚረዳ መሆኑን እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባው፡-

ሀ) ሀሰተኛ ሰነድ ያዘጋጀ፣ ያቀረበ ወይም የሰጠ እንደሆነ፤

ለ) የሙያ፣ የልምድ፣ የሞራል ምክር ወይም ድጋፍ የሰጠ እንደሆነ፤

ሐ) ማናቸውንም ዓይነት ንብረት በማናቸውም ሁኔታ ያቀረበ፣ ያሰባሰበ ወይም እንዲቀርብ ያደረገ እንደሆነ፤

መ) የገንዘብ ወይም የፋይናንስ ወይም ሌሎች ተያያዥነት ያላቸው አገልግሎቶችን ያቀረበ ወይም የሰጠ እንደሆነ፤

ሠ) ማናቸውንም ፈንጂ፣ ዳይናሚት፣ ሊቀጣጠል የሚችል ነገር፣ የጦር መሳሪያ ወይም ሌላ ገዳይነት ያለው መሳሪያ ወይም መርዛማ ነገር ያቀረበ ወይም የሰጠ እንደሆነ፤ ወይም

ረ) ማናቸውም አይነት ሥልጠና ወይም ትምህርት ወይም መመሪያ የሰጠ እንደሆነ፤

ከ፲ እስከ ፲፭ አመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

5/ causes damage to natural resource, environment, historical or cultural heritages;

6/ endangers, seizes or puts under control, causes serious interference or disruption of any public service; or

7/ threatens to commit any of the acts stipulated under sub-articles (1) to (6) of this Article;

is punishable with rigorous imprisonment from 15 years to life or with death.

## 4. Planning, Preparation, Conspiracy, Incitement and Attempt of Terrorist Act

Whosoever plans, prepares, conspires, incites or attempts to commit any of the terrorist acts stipulated under sub-articles (1) to (6) of Article 3 of this Proclamation is punishable in accordance with the penalty provided for under the same Article.

## 5. Rendering Support to Terrorism

1/ Whosoever, knowingly or having reason to know that his deed has the effect of supporting the commission of a terrorist act or a terrorist organization:

a) provides, prepares or gives forged or falsified document;

b) provides a skill, expertise or moral support or gives advice;

c) provides, collects or makes available any property in any manner;

d) provides or makes available monetary, financial or other related services;

e) provides or makes available any explosive, dynamite, inflammable substances, firearms or other lethal weapons or poisonous substances; or

f) provides any training or instruction or directive;

is punishable with rigorous imprisonment from 10 to 15 years.

፪/ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ የተመለከተ የሽብርተኝነት ድርጊት የፈፀመ መሆኑን እያወቀ ለማንኛውም ሰው ከለላ የሰጠ ወይም እንዲያመልጥ የረዳ ወይም የደበቀ እንደሆነ ከ፲ ዓመት እስከ እድሜ ልክ በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

2/ Whosoever harbors or helps to escape or conceals someone whom he knows to have committed terrorist act mentioned under this Proclamation is punishable with rigorous imprisonment from 10 years to life.

### ፮. ሽብርተኝነትን ስለማበረታታት

ማንኛውም ሰው መልእክቱ እንዲታተምላቸው የተደረገው የህብረተሰቡ አባላት በከፊል ወይም በሙሉ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፫ የተመለከተ ማናቸውንም የሽብርተኝነት ድርጊት እንዲፈጽሙ ወይም ለመፈጸም እንዲዘጋጁ ወይም እንዲነሳሱ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ የሚያበረታ ታቸው ወይም በማናቸውም ሌላ ሁኔታ የሚገፋ ፋቸው እንደሆነ አድርገው ይረዱታል ተብሎ ሊገመት የሚችል መልዕክት ሆነ ብሎ ወይም በግዴለሽነት ያተመ ወይም ያሳተመ እንደሆነ ከ፲ እስከ ፳ ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

### 6. Encouragement of Terrorism

Whosoever publishes or causes the publication of a statement that is likely to be understood by some or all of the members of the public to whom it is published as a direct or indirect encouragement or other inducement to them to the commission or preparation or instigation of an act of terrorism stipulated under Article 3 of this Proclamation is punishable with rigorous imprisonment from10 to 20 years.

### ፯. በሽብርተኛ ድርጅት ውስጥ ስለመሳተፍ

፩/ ማንኛውም ሰው ለሽብርተኛ ድርጅት ወይም የሽብርተኝነት ድርጊቶችን ለመፈፀም ሰው የመለመለ ወይም አባል የሆነ ወይም ስልጠና የወሰደ ወይም በድርጅቱ በማናቸውም መልክ የተሳተፈ እንደሆነ እንደየተሳትፎ ደረጃው ከ፭ እስከ ፲ አመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

፪/ ማንኛውም ሰው በሽብርተኛ ድርጅት ውስጥ በአመራርነት ወይም በውሳኔ ሰጪነት የሰራ እንደሆነ ከ፳ ዓመት እስከ እድሜ ልክ በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

### 7. Participation in a Terrorist Organization

1/ Whosever recruits another person or takes training or becomes a member or participates in any capacity for the purpose of a terrorist organization or committing a terrorist act, on the basis of his level of participation, is punishable with rigorous imprisonment from 5 to 10 years.

2/ Whosever serves as a leader or decision maker in a terrorist organization is punishable with rigorous imprisonment from 20 years to life.

### ፰. ለሽብርተኝነት ድርጊት መፈፀሚያነት እንዲውል ንብረት መያዝ ወይም መጠቀም

ማንኛውም ሰው የሽብርተኝነት ድርጊት ለመፈፀም ወይም እንዲፈጸም ለማመቻቸት እንደሚውል እያወቀ ወይም እንዲውል በማሰብ ማናቸውንም ንብረት የያዘ ወይም የተጠቀመ እንደሆነ፣ የንብረቱ መወረስ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከ፭ እስከ ፳ ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

### 8. Possessing or Using Property for Terrorist Act

Whosoever possesses or uses property knowing or intending it to be used to committing or facilitating a terrorist act is punishable, subject to the property being forfeited, with rigorous imprisonment from 5 to 20 years.

### ፱. በሽብርተኝነት ድርጊት የተገኘን ንብረት ስለመያዝና መገልገል

ማንኛውም ሰው ከሽብርተኝነት ድርጊት የተገኘ ንብረት መሆኑን እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባው አንድን ንብረት በባለቤትነት የያዘ ወይም በይዞታው ስር ያደረገ ወይም የተጠቀመ ወይም የለወጠ ወይም የደበቀ ወይም ያመሳሰለ እንደሆነ፣ የንብረቱ መወረስ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከ፭ እስከ ፲፭ ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

### 9. Possessing and Dealing with Proceeds of Terrorist Act

Whosoever knowingly or having reason to know that a property is a proceed of terrorist act acquires or possesses or owns or deals or converts or conceals or disguises the property is punishable, subject to the property being forfeited, with rigorous imprisonment from 5to 15 years.

**፲. ምስክር ማባበል ወይም ማስፈራራትና ማስረጃ ማጥፋት**

ማንኛውም ሰው፣

፩/ በሽብርተኝነት ድርጊት ላይ ምስክር የሆነን ወይም ለመሆን የሚችል ሰውን እንዳይ መሰክር የደለለ ወይም ያስፈራራ ወይም በምስክሩ ወይም ከምስክሩ ጋር የቅርብ ግንኙነት ባለው ሰው ላይ የሀይል ድርጊት የፈፀመ እንደሆነ፣ ወይም

፪/ ማስረጃ ያጠፋ ወይም የደበቀ እንደሆነ፣

ከ፭ እስከ ፳ ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል።

**፲፩. በሀሰት የሽብርተኝነት ድርጊት ስለማስፈራራት**

ማንኛውም ሰው ሀሰተኛ መሆኑን እያወቀ ወይም እያመነ የሽብርተኝነት ድርጊት እንደተፈፀመ ወይም እየተፈፀመ እንደሆነ ወይም እንደሚፈፀም በማናቸውም መንገድ ለሌላ ሰው ሆን ብሎ የገለፀ እንደሆነ ከ፫ እስከ ፲ ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል።

**፲፪. የሽብርተኝነት ድርጊቶችን አለማስታወቅ**

ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ የተመለከተ የሽብርተኝነት ድርጊት ሳይፈፀም ለመከላከል የሚረዳ መረጃ እያለው ወይም የሽብርተኝነት ድርጊትን የፈፀመን ወይም ሊፈፅም የተዘጋጀን ሰው ለመያዝ ወይም ለመክሰስ ወይም ለማስቀጣት የሚያስችል መረጃ ወይም ማስረጃ እያለው ያለበቂ ምክንያት መረጃውን ወይም ማስረጃውን ለፖሊስ ወዲያውኑ ያልገለፀ ወይም ሀሰተኛ መረጃ የሰጠ እንደሆነ ከ፫ እስከ ፲ ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል።

**ክፍል ሦስት**

**የመከላከልና የምርመራ እርምጃዎች**

**፲፫. ለሽብርተኝነት ጥቃት የተጋለጡ ሰዎችን ስለ ማዳን**

፩/ ፖሊስ በአንድ የተወሰነ ቦታ ላይ የሽብር ተኝነት ድርጊት የተፈፀመ ወይም እየተፈፀመ ለመሆኑ ወይም ሊፈፀም እንደሚችል ወይም በዚሁ አካባቢ ያሉ ሰዎች ለሽብርተኝነት ጥቃት የተጋለጡ ወይም ሊጋለጡ እንደ ሚችሉ በቂ ምክንያት ሲኖረው፡-

ሀ) በአካባቢው ያሉ ሰዎች ወደ አንድ ሥፍራ እንዲገቡ ወይም እንዳይገቡ ወይም ሥፍራውን እንዲለቁ ወይም በተገለለ ቦታ እንዲቆዩ፤

**10. Inducing or Threatening Witness and Destroying Evidence**

Whosoever:

1/ induces or threatens a person who is or can be a witness for an act of terrorism or uses violence against the witness or a person who has close relationship with the witness to prevent the witness from testifying; or

2/ destroys or hides evidence;

is punishable with rigorous imprisonment from 5 to 20 years.

**11. False Threat of Terrorist Act**

Whosoever while knowing or believing that the information is false, intentionally communicates or makes available by any means that a terrorist act has been or is being or will be committed, is punishable with rigorous imprisonment from 3 to 10 years.

**12. Failure to Disclose Terrorist Acts**

Whosoever, having information or evidence that may assist to prevent terrorist act before its commission, or having information or evidence capable to arrest or prosecute or punish a suspect who has committed or prepared to commit an act of terrorism, fails to immediately inform or give information or evidence to the police without reasonable cause, or gives false information, is punishable with rigorous imprisonment from 3 to 10 years.

**PART THREE**

**PREVENTIVE AND INVESTIGATIVE MEASURES**

**13. Protecting Individuals Exposed to Terrorist Attacks**

1/ A police officer, having reasonable grounds to believe that a terrorist act has been or is being or will be committed in a particular place, or that people around such place are exposed or may be exposed to terrorist attacks, may:

a) order people around the place to enter into a premise or prevent their entry into a premise or order them to evacuate a premise or keep them in a secluded area;

ለ) ለአደጋው ምንጭ የሆነው ወይም ሊሆን የሚችለው ዕቃ እንዲወድም፣ እንዲ ወሰድ ወይም ከነበረበት ቦታ እንዲነሳ፤

ሐ) ሰዎችን ከመመረዝ ለማዳን ተገቢ የሆኑ ትእዛዞችን እንዲፈፅሙ፤

መ) የተመረዘው ቤት ወይም ቦታ በቁጥጥር ስር እንዲውል፤ ወይም

ሠ) አደጋውን ወይም መመረዙን ለመከላከል ወይም ለመቀነስ የሚያስችል ማንኛውም እርምጃ እንዲወሰድ፤

የፅሁፍ ወይም የቃል ትእዛዝ ለመስጠትና ይህንንም ለማስፈፀም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገ- ኘው የማስገደድ እርምጃ ሊወስድ ይችላል::

፪/ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) የተሰጠ ትእዛዝ በፖሊስ በሚነገር ማስታወቂያ ሊነሳ ወይም ሊራዘም ይችላል::

፫/ ለሽብርተኝነት አደጋ የተጋለጠ ማንኛውም ሰው ፖሊስ የሰጠውን ትእዛዝ የመፈፀምና የመተባበር ግዴታ አለበት:: እንዲሁም የህንፃ፣ የምድረ ግቢ ወይም ሥፍራ ባለቤት ወይም አስተዳዳሪ የሆነ ሰው በዚህ አንቀጽ መሠረት የተሰጠውን ትእዛዝ የማስፈፀም ኃላፊነት አለበት::

፬/ መንግስት እንደ አስፈላጊነቱ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ማናቸውም አምራች ወይም አገልግሎት ሰጪ ተቋም ከድንገተኛ አደጋ ሰውን ለማዳን እቅድ እንዲኖረው ሊያደርግ ይችላል::

## ፲፬. መረጃ ስለማሰባሰብ

፩/ የሽብርተኝነት ድርጊትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የብሔራዊ የመረጃና ደህንነት አገልግሎት ከፍርድ ቤት ፈቃድ በመውሰድ፡-

ሀ) በሽብርተኝነት ወንጀል የተጠረጠረን ሰው የስልክ፣ የፋክስ፣ የሬድዮ፣ የኢንተር ኔት፣ የኤሌክትሮኒክስ፣ የፖስታና የመሳ ሰሉ ግንኙነቶችን ለመጥለፍ ወይም ለመ ከታተል፤

ለ) ጠለፋውን ለማስፈፀም ወደ ማናቸውም ቤት ውስጥ በሚስጥር ለመግባት፤ ወይም

ሐ) ይህንኑ ለመፈፀም የሚያስችሉ መሳሪያ ዎችን ለማስቀመጥ ወይም ለማንሳት፤

ይችላል::

፪/ በጠለፋ የሚገኝ መረጃ በምስጢር መጠበቅ አለበት::

b) destroy, take away or remove the thing which is or may be a source of the danger;

c) order individuals to follow any procedures which protects them from poisoning;

d) put under control the contaminated building or land; or

e) take any measure that enable to prevent or reduce the danger or contamination;

by issuing oral or written order and, if necessary, by using compeling measure.

2/ An order given under sub-article (1) of this Article, may be lifted or extended by way of police annocument.

3/ Any individual exposed to danger of terrorism shall have the duty to execute and cooperate in the execution of the order given by the police. Furthermore, an owner or person in charge of any building or premise, or place shall have the duty to enforce the order given under this Article.

4/ The government, when finds it necessary, may, by issuing a directive, make any manufacturing or service rendering institution to have contingency plan in order to save people from danger in case of emergency.

## 14. Gathering Information

1/ To prevent and control a terrorist act, the National Intelligence and Security Service may, up on getting court warrant:

a) intercept or conduct surveillance on the telephone, fax, radio, internet, electronic, postal and similar communications of a person suspected of terrorism;

b) enter into any premise in secret to enforce the interception; or

c) install or remove instruments enabling the interception.

2/ Information obtained through interception shall be kept in secret.

፫/ ማናቸውም የመገናኛ አገልግሎት አቅራቢ በብሔራዊ የመረጃና ደህንነት አገልግሎት ጠለፋውን ለማካሄድ ሲጠየቅ አስፈላጊውን ትብብር ማድረግ አለበት።

፬/ የሽብርተኝነት ድርጊትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የብሔራዊ የመረጃና ደህንነት አገልግሎት ወይም ፖሊስ ክትትል በማድረግ መረጃዎችን ሊያሰባስብ ይችላል።

3/ Any communication service provider shall cooperate when requested by the National Intelligence and Security Service to conduct the interception.

4/ The National Intelligence and Security Services or the Police may gather information by surveillance in order to prevent and control acts of terrorism.

## ፲፭. ተከራይን ስለሚመለከቱ መረጃዎች

፩/ ማንኛውም ቤት፣ ቦታ፣ ክፍል ወይም ተሽከርካሪ ወይም ተመሳሳይ መገልገያ አከራይ የሆነ ሰው የተከራዩን ማንነት በዝርዝርና በፅሁፍ የመያዝ እና በአቅራቢያው ላለ ፖሊስ ጣቢያ በሃያ አራት ሰአት ውስጥ የማሳወቅ ግዴታ አለበት።

፪/ ማንኛውም ሰው በቤቱ ውስጥ የውጭ ሀገር ዜጋን ሲያኖር በአቅራቢያው ላለ ፖሊስ ጣቢያ ስለሚያኖረው ሰው ማንነት ዝርዝር መግለፅና የፓስፖርቱን ኮፒ የማቅረብ ግዴታ አለበት።

## 15. Information about a Lessee

1/ Whosoever leases a house, place, room, vehicle or any similar facility shall have the duty to register in detail the identity of the lessee and notify the same to the nearest police station within 24 hours.

2/ Any person, who lets a foreigner live in his house, shall have a duty to notify the nearest police within 24 hours, about the identity of the foreigner and submit a copy of his passport.

## ፲፮. ድንገተኛ ፍተሻ

ፖሊስ የሽብርኝነት ድርጊት ሊፈፀም እንደሚችል በቂ ጥርጣሬ ሲኖረውና ድርጊቱን ለመከላከል ድንገተኛ ፍተሻ ማድረግ አስፈላጊ ነው ብሎ ሲያምን በፌዴራል ፖሊስ ዋና ዳይሬክተር ወይም እርሱ በሚወክለው ሀላፊ ፈቃድ በአካባቢው ያለን ተሽከርካሪ እና እግረኞችን በማስቆም በማንኛውም ጊዜ በድንገት ለመፈተሽና አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ለመያዝ ይችላል።

## 16. Sudden Search

Where a police officer has reasonable suspicion that a terrorist act may be committed and deems it necessary to make a sudden search in order to prevent the act, with the permission of the Director General of the Federal Police or a person delegated by him, may stop vehicle and pedestrian in an area and conduct sudden search at any time, and seize relevant evidences.

## ፲፯. በድብቅ የሚደረግ ብርበራ

ፖሊስ፣

፩/ የሽብር ድርጊት የተፈፀመ እንደሆነ ወይም ሊፈፀም እንደሚችል፣ ወይም

፪/ በሚበረብረው ቤት ውስጥ ነዋሪ ወይም ባለ ይዞታ የሆነው ሰው የሽብርተኝነት ድርጊት ለመፈፀም ዝግጅት ስለማድረጉ ወይም ዕቅድ ስለመንደፉ፣ እና

፫/ የሚደረገው ብርበራ የሽብርተኝነት ድርጊት ወይም በሽብርተኝነት ድርጊት የሚጠረጠር እንቅስቃሴን አስቀድሞ ለመከላከል ወይም እርምጃ ለመውሰድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንደሚኖረው፣

በበቂ ምክንያት ያመነ ከሆነ በድብቅ የሚደረግ የብርበራ ማዘዣ ከፍርድ ቤት እንዲሰጠው በፅሁፍ ወይም አስቸኳይ ሁኔታ ሲኖር በስልክ ፈቃድ ሊጠይቅ ይችላል።

## 17. Covert Search

A police may request the court in writing or, in urgent cases, by telephone for covert search warrant where he has reasonable grounds to believe that:

1/ a terrorist act has been or is likely to be committed; or

2/ a resident or possessor of a house to be searched has made preparations or plans to commit a terrorist act; and

3/ covert search is essential to prevent or to take action against a terrorist act or suspected terrorist activity.

**፲፰. በድብቅ የሚደረግ ብርበራ ለማካሄድ ስለሚሰጥ ትእዛዝ**

፩/ ፍርድ ቤቱ በአመልካች በሚቀርብለት መረጃ መሰረት፣

ሀ) የተፈጸመውን ወይም የተጠረጠረውን የሽብር ድርጊት ባህሪ ወይም አደገኛነት፣ እና

ለ) በማዘዣው መሰረት የሚወሰደው እርምጃ የሽብር ድርጊቱን ለመከላከል ወይም ተጠርጣሪውን በቁጥጥር ስር ለማዋል የሚኖረውን አስተዋፅኦ፣

ከግምት ውስጥ በማስገባት በድብቅ የሚደረግ ብርበራ ማዘዣ ይሰጣል::

፪/ በዚህ አንቀጽ መሰረት የሚሰጥ ማዘዣ:-

ሀ) ማዘዣው የሚመለከተውን ቤት አድራሻና የሚታወቅ ከሆነ የቤቱን ነዋሪዎች ስም፣

ለ) ከፍተኛው ሠላሳ ቀናት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ማዘዣው ተፈፃሚ የሚሆንበትን ጊዜና ማዘዣው የተሰጠበትን ቀን፣ እና

ሐ) እንደ አስፈላጊነቱ የሚበረበሩትንና የሚያዙትን ማስረጃዎች አይነት ወይም ዝርዝር፣

መያዝ አለበት::

**፲፱. የመያዝ ሥልጣን**

፩/ በዚህ አዋጅ የተመለከተ የሽብርተኝነት ድርጊት ለመፈፀሙ ወይም እየፈፀመ ያለ ስለመሆኑ በሚገባ የሚጠረጥረውን ማንኛውንም ሰው ያለ ፍርድ ቤት ትእዛዝ ፖሊስ ለመያዝ ይችላል::

፪/ የተያዘው ሰው በ፵፰ ሰዓታት ውስጥ ፍርድ ቤት የመቅረብ መብት አለው:: ይህም ጊዜ ከተያዘበት ቦታ ወደ ፍርድ ቤት ለመድረስ አግባብ ባለው ግምት የሚጠይቀውን ጊዜ አይጨምርም::

**፳ በእስር የማቆያ ትእዛዝ**

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፱ በተመለከተው መሠረት የተያዘ ሰው የቀረበለት ፍርድ ቤት ለምርመራ ወይም ክሱን በፍርድ ቤት ለመስማት የተያዘው ሰው በማረፊያ ቤት እንዲቆይ ሊወስን ይችላል::

፪/ ምርመራው ያልተጠናቀቀ እንደሆነ መርማሪው ፖሊስ ምርመራውን የሚፈጽምበት በቂ ጊዜ እንዲሰጠው ፍርድ ቤቱን መጠየቅ ይችላል::

**18. Warrant Given to Conduct Covert Search**

1/ The court on the basis of the information presented to it by the applicant, may give covert search warrant by having into consideration:

a) the nature or gravity of the terrorist act or the suspected terrorist act; and

b) the extent to which the measures to be taken in accordance with the warrant would assist to prevent the act of terrorism or arrest the suspect.

2/ A warrant issued in accordance with this Article shall specify:

a) the address of any premise to which the warrant relates, and the names of the occupiers, if known;

b) the maximum duration being 30 days, the period during which the warrant is valid and the date on which the warrant is issued; and

c) if necessary, the type or description of evidences to be searched for and seized.

**19. Powers of Arrest**

1/ The police may arrest without court warrant any person whom he reasonably suspects to have committed or is committing a terrorist act as provided under this Proclamation.

2/ The arrested person shall have the right to be brought before a court within 48 hours of his arrest. Such time shall not include the time reasonably required for the journey from the place of arrest to the court.

**20. Detention and Remand Order**

1/ The court, before which an arrested person is presented in accordance with Article 19 of this Proclamation, may give an order to remand the suspect for investigation or trial.

2/ If the investigation is not completed, the investigating police officer may request the court for sufficient period to complete the investigation.

፫/ በማረፊያ ቤት ለምርመራ ለማቆየት የሚሰጠው እያንዳንዱ ጊዜ ቢያንስ ለ፳፰ ቀናት ይሆናል፤ ሆኖም በአጠቃላይ የሚሰጠው ጊዜ ከአራት ወራት መብለጥ አይኖርበትም።

፬/ በዋስትና ጉዳዮች ላይ ዐቃቤ ህግ ይግባኝ ለማቅረብ ይችላል።

፭/ በዚህ አዋጅ መሰረት በሽብርተኝነት ወንጀል ክስ የቀረበ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ክሱን ሰምቶ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ ተከሳሹ በማረፊያ ቤት እንዲቆይ ያዛል።

## ፳፩. ናሙናዎችን የመስጠት ግዴታ

ፖሊስ በሽብርተኝነት ወንጀል ጉዳይ የተጠረጠረ ሰው የእጅ ጽሑፉን፣ የጣት አሻራውን፣ ፎቶግራፉን፣ የፀጉሩን፣ የድምፁን፣ የደሙን፣ የምራቁንና ሌሎች በሰውነቱ የሚገኙ ፈሳሽ ነገሮችን ናሙናዎች ለምርመራ እንዲሰጥ ሊያዝ ይችላል። በተጨማሪም የህክምና ምርምራ እንዲያደርግ ሊያዝ ይችላል። ተጠርጣሪው ለምርመራው ፈቃደኛ ካልሆነ ፖሊስ አስፈላጊ የሆነ ተመጣጣኝ ሀይል ተጠቅሞ ከተጠርጣሪው ናሙና ሊወስድ ይችላል።

## ፳፪. መረጃ የመስጠት ግዴታ

የሽብርተኝነት ወንጀል ለመከላከል ወይም ምርመራ ለማከናወን ፖሊስ ለምርመራው የሚረዳው መሆኑን በሚገባ የሚያምንበትን መረጃ ወይም ማስረጃ ከማናቸውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት፣ ባለሥልጣን፣ ባንክ፣ የግል ድርጅት ወይም ግለሰብ እንዲሰጠው ሊጠይቅ ይችላል። መረጃ ወይም ማስረጃ የተጠየቀው ወገን መረጃውን ወይም ማስረጃውን የመስጠት ግዴታ አለበት።

## ክፍል አራት

## የማስረጃና የሥነሥርዓት ደንቦች

## ፳፫. ተቀባይነት ስለሚኖራቸው ማስረጃዎች

በወንጀለኛ መቅጫ ሥነሥርዓት ህግና ሌሎች አግባብነት ባላቸው ህጎች የሚቀርቡ ማስረጃዎች ተቀባይነታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት ማስረጃዎች በሽብርተኝንት ጉዳዮች በፍርድ ቤት በማስረጃነት ተቀባይነት ይኖራቸዋል፡-

፩/ የመረጃውን ምንጭ ወይም መረጃው እንዴት እንደተገኘ ባይገልጽም በሽብርተኝነት ወንጀል የተዘጋጀ የመረጃ ሪፖርት፤

፪/ የሰሚ ሰሚ ወይም በተዘዋዋሪ የተገኙ ማስረጃዎች፤

፫/ ዲጂታል ወይም ኤሌክትሮኒክ ማስረጃዎች፤

3/ Each period given to remand the suspect for investigation shall be a minimum of 28 days; provided however, that the total time shall not exceed a period of four months.

4/ Public prosecutor may appeal on bail cases.

5/ If a terrorism charge is filed in accordance with this Proclamation, the court shall order the suspect to be remanded for trial until the court hears and gives decision on the case.

## 21. Duty to Giving Samples

The police may order a person suspected of acts of terrorism to give samples of his hand writing, hair, voice, finger print, photograph, blood, saliva and other body fluids, for investigation. Moreover, he may order the suspect to undergo medical test. If the suspect is not willing for the test, the police may use necessary and reasonable force to take samples.

## 22. Duty to Give Information

The police may request from any government institution, official, bank or a private organization or an individual to be given information or evidence which he reasonably believes could assist to prevent or investigate terrorism cases. Any one so requested shall have the duty to give the information or evidence.

## PART FOUR

## EVIDENTIARY AND PROCEDURAL RULES

## 23. Admissible Evidences

Without prejudice to the admissibility of evidences to be presented in accordance with the Criminal Procedure Code and other relevant legislations, the following shall be admissible in court for terrorism cases:

1/ intelligence report prepared in relation to terrorism, even if the report does not disclose the source or the method it was gathered;

2/ hearsay or indirect evidences;

3/ digital or electronic evidences;

፬/ በጠለፋ ወይም በክትትል የተገኙ ማስረጃዎች ወይም በውጭ ሀገር የህግ አስከባሪ አካላት በተደረገ ጠለፋ የተገኙ መረጃዎች፤ እና

፭/ በሽብርተኝነት ድርጊት ከሚጠረጠር ሰው በፅሑፍ፣ በድምፅ መቅረጫ፣ በቪድዮ ካሴት፣ ወይም በማናቸውም ሌላ ሜካኒካል ወይም ኤሌክትሮኒክ መሳሪያ የተቀረፀ የእምነት ቃል፡፡

**፳፬. <u>የሽብርተኝነት ወንጀል በይርጋ የማይታገድ ስለመሆኑ</u>**

በዚህ አዋጅ የተመለከተ ማናቸውንም የሽብርተኝነት ወንጀል በፈፀመ ሰው ላይ የሚቀርብ ክስ በይርጋ አይታገድም፡፡

## ክፍል አምስት

## የሽብርተኛ ድርጅቶችንና ከሽብርተኝነት ድርጊት የተገኙ ንብረቶችን የመቆጣጠር እርምጃዎች

**፳፭. <u>ድርጅት በሽብርተኝነት ስለሚሰየምበት ሥርዓት</u>**

፩/ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በመንግስት አቅራቢነት አንድን ድርጅት በሽብርተኝነት የመሰየም እና የሽብርተኝነቱን ስያሜን የመሻር ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

፪/ ማንኛውም ድርጅት በሽብርተኛ ድርጅትነት የሚሰየመው በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ፡-

ሀ) የሽብርተኝነት ወንጀል ከፈጸመ፤

ለ) የሽብርተኝነት ወንጀል ለመፈፀም ከተዘጋጀ፤

ሐ) ሽብርተኝነትን ከደገፈ ወይም ካበረታታ፤ ወይም

መ) በሌላ መንገድ ከሽብርተኝነት ጋር ተያያዥነት ያለው ሆኖ ከተገኘ፤

ይሆናል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) መሰረት በሽብርተኝነት የተሰየመ ድርጅት ህጋዊ ሰውነቱን ያጣል፡፡

፬/ በዚህ አዋጅ መሰረት የሚቋቋመውን የሽብር ተኝነት ተጎጂዎች ፈንድ የሚያስተዳድረው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት ህጋዊ ህልውናውን ላጣ ድርጅት ንብረት አጣሪ ይመድባል፤ የማፍረስ ሂደቱን ያስፈፅማል፡፡

4/ evidences gathered through interception or surveillance or information obtained through interception conducted by foreign law enforcement bodies; and

5/ confession of a suspect of terrorism in writing, voice recording, video cassette or recorded in any mechanical or electronic device.

**24. <u>Inapplicability of Statue of Limitation for Terrorism Cases</u>**

Criminal liability of persons who commit terrorism crimes as stipulated under this Proclamation shall not be barred by statue of limitations.

## PART FIVE

## MEASURES TO CONTROL TERRORIST ORGANIZATIONS AND PROPERTY

**25. <u>Procedure of Proscribing Terrorist Organization</u>**

1/ The House of Peoples' Representatives shall have the power, upon submission by the government, to proscribe and de-proscribe an organization as terrorist organization.

2/ Any organization shall be proscribed as terrorist organization if it directly or indirectly:

a) commits acts of terrorism;

b) prepares to commit acts of terrorism;

c) supports or encourages terrorism; or

d) is otherwise involved in terrorism.

3/ Where any organization is proscribed as terrorist in accordance with sub-article (1) and (2) of this Article, its legal personality shall cease.

4/ The body that administers the terrorism victims fund to be established in accordance with this Proclamation shall assign a liquidator to the organization the legal personality of which has ceased pursuant to sub-article (3) of this Article, and enforce the process of the liquidation.

## ፳፮. የሽብርተኛ ንብረት ስለማገድና ስለመያዝ

፩/ ፖሊስ በሚያካሂደው ምርመራ የባንክ ሂሳብን ጨምሮ ማናቸውም ንብረት በዚህ አዋጅ የተመለከተ የሽብርተኝነት ወንጀል የተፈፀመበት ወይም ሊፈፀምበት እንደሚችል በሚገባ የጠረጠረ እንደሆነ ከፍርድ ቤት በሚያገኘው ፈቃድ መሰረት ንብረቱን በቁጥጥሩ ስር ለማድረግ ይችላል፡፡

፪/ ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት በሚሰጠው ትዕዛዝ የተጠቀሰው ንብረት ለሌላ ሦስተኛ ወገን እንዳይተላለፍና ማናቸውም ሌላ ሕጋዊ ግንኙነት እንዳይፈጸምበት ጊዜያዊ የእግድ ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡

፫/ የእግዱ ትዕዛዝ ግልባጭ ለሚመለከተው የአስተዳደር መሥሪያ ቤትና ለንብረቱ ባለቤት ወይም ባለይዞታ እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡

፬/ የተያዘው ወይም የእግድ ትዕዛዝ የተጣለበት ንብረት ባለቤት ወይም ባለይዞታ ቅር የተሰኘ እንደሆነ ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡

፭/ ፍርድ ቤቱ ንብረቱ የተያዘው ወይም የታገደው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) መሰረት አለመሆኑን ሲያረጋግጥ ንብረቱ እንዲለቀቅ ወይም ዕግዱ እንዲነሳ ማድረግ ይችላል፡፡

## ፳፯. የሽብርተኛ ንብረት ስለመውረስ

፩/ በሽብርተኝነት ድርጊት የተገኘ ንብረት ወይም የሽብርተኛ ድርጅት ወይም የሽብርተኛ ንብረት በመንግሥት ይወረሳል፡፡

፪/ የሽብርተኛ ንብረት እንዲወረስ ለማድረግ በጉዳዩ ላይ የወንጀል ክስ ቀርቦ እንደሆነ በዚሁ የክስ መዝገብ ዐቃቤ ህግ መጠየቅ ይችላል፡፡ የወንጀል ክስ ባልተመሰረተበት ሁኔታ ማመልከቻው ለብቻው መዝገብ ተከፍቶለት ለፍርድ ቤቱ ይቀርባል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የመውረስ ትእዛዝ ከመሰጠቱ በፊት ፍርድ ቤቱ በተጠቀሰው ንብረት ላይ መብት ወይም ጥቅም አለኝ ለሚል ማንኛውም ሰው የመሰማት እድል መስጠት ይኖርበታል፡፡

፬/ የተወረሰው ንብረት በዚህ አዋጅ መሠረት ወደ ተቋቋመው የሽብርተኝነት ተጎጂዎች ፈንድ ገቢ ይደረጋል፡፡

## 26. Freezing and Seizure of Terrorist Property

1/ Where the police, while conducting investigation, has reasonable ground to suspect that any property including bank account has been or may be used to commit terrorist act as stipulated under this Proclamation, he may seize the property in accordance with court authorization.

2/ The court shall, in the authorization issued pursuant to sub-article (1) of this Article, pass a temporary freezing order to prevent the transfer of such property to a third party and any other legal transactions involving such property.

3/ A copy of the freezing order shall be given to the concerned administrative office and to the owner or possessor of the property.

4/ If the owner or possessor of the seized or frozen property is aggrieved by the order, he may lodge an appeal.

5/ When the court finds that the property was seized or frozen contrary to the provisions of sub-article (1) and (2) of this Article, it may order the release of the property or the lifting of the freezing.

## 27. Forfeiture of Terrorist Property

1/ Proceeds of terrorism or property of a terrorist organization or a terrorist shall be forfeited by the government.

2/ Where a criminal charge is instituted on the matter the public prosecutor may request for an order of forfeiture within the same criminal charge file. If criminal charge is not instituted the application may be presented to the court under a separate file.

3/ Before making forfeiture order under sub-article (1) of this Article, the court shall give every person appearing to have an interest in the property an opportunity to be heard.

4/ The property shall be transferred to the terrorism victims fund established in accordance with this Proclamation.

## ክፍል ስድስት

## የሽብርተኝነት ጉዳይ የሚከታተሉ ተቋማት

### ፳፰. የሽብርተኝነት ድርጊትን ስለሚከታተል ዐቃቤ ሕግና ፖሊስ

፩/ በሕግ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የሽብርተኝነት የወንጀል ጉዳይን የሚከታተል ዐቃቤ ሕግ ወይም ፖሊስ፡-

ሀ) አግባብነት ባለው ሙያ ቢያንስ ከአምስት ዓመት በላይ የሥራ ልምድ ያለው፣ ሥልጠና የወሰደና በሥራው ታታሪ የሆነ፤ እና

ለ) እንደ አግባብነቱ ከፍትህ ሚኒስቴር ወይም ከፌዴራል ፖሊስ የበላይ ኃላፊዎች የሙያ ብቃትና የሥነ ምግባር ማረጋገጫ ምስክርነት ያገኘ፣

መሆን አለበት፡፡

፪/ የፍትህ ሚኒስቴር የሽብርተኝነት ጉዳዮችን የሚከታተል የተለየ የሥራ ክፍል ያደራጃል፡፡

፫/ የፌዴራል ፖሊስ የሽብርተኝነት ጉዳዮችን የሚከታተል የተለየ የሥራ ክፍል ያደራጃል፡፡

### ፳፱. የሽብርተኝነት ጉዳይ ስለሚከታተሉ የደህንነት ሠራተኞች

በብሔራዊ የመረጃና ደህንነት አገልግሎት የሽብርተኝነት ጉዳዮችን የሚከታተሉ የመሥሪያ ቤቱ ሠራተኞችን መርጦ ይመድባል፡፡ የሽብርተኝነት ጉዳይን የሚከታተል የተለየ የሥራ ክፍል ያደራጃል፡፡

### ፴. ስለብሔራዊ የፀረ ሽብርተኝነት አስተባባሪ ኮሚቴ

፩/ የሽብርተኝነት ድርጊትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የፍትሕ ሚኒስቴር፣ የብሔራዊ የመረጃና ደህንነት አገልግሎት እና የፌዴራል ፖሊስ መሥሪያ ቤት ኃላፊዎችን ያቀፈ ብሔራዊ የፀረ ሽብርተኝነት አስተባባሪ ኮሚቴ ይዋቀራል፡፡

፪/ የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር ኮሚቴውን ይመራል፡፡

፫/ ኮሚቴው የጋራ የፀረ ሽብርተኝነት እቅድ ያወጣል፣ የጋራ የፀረ ሽብርተኝነት ግብረ ሀይል በማደራጀት ተቋሞቹ ሽብርተኝነትን ለመዋጋት የሚያደርጉትን ጥረት በማቀናጀት በጋራና በተደጋጋፊነት እንዲሠሩ ያደርጋል፡፡

## PART SIX

## INSTITUTIONS THAT FOLLOW UP CASES OF TERRORISM

### 28. Prosecutor and Police Following up Cases of Terrorism

1/ A public prosecutor or police officer who follows up terrorism cases in accordance with the powers conferred up on by law shall:

a) have more than five years of relevant work experience and the appropriate training and be hard working; and

b) have obtained testimonials from the relevant senior officials of the Ministry of Justice or the Federal Police as to his professional competency and ethics.

2/ The Ministry of Justice shall organize a separate specialized department which follow up terrorism cases.

3/ The Federal Police shall organize a separate specialized department which follow up terrorism cases.

### 29. Intelligence Personnel Following up Cases of Terrorism

The National Intelligence and Security Service shall select and assign officers who follow up cases of terrorism. It shall organize a separate specialized department which follow up terrorism cases.

### 30. National Anti-Terrorism Coordinating Committee

1/ In order to prevent and control terrorist acts a National Anti-Terrorism Coordination Committee comprising the heads of the Ministry of Justice, National Intelligence and Security Service and Federal Police shall be established.

2/ The Director General of the National Intelligence and Security Service shall lead the Committee.

3/ The Committee shall draw up joint counter terrorism plan and set up joint counter terrorism task force and shall work together in coordinating their efforts.

## ፴፩. በሽብርተኝነት ወንጀል የዳኝነት ሥልጣን

፩/ የፌዴራል ከፍተኛና ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች:-

ሀ) በዚህ አዋጅ መሠረት የሚቀርቡ ጉዳዮችን፣

ለ) በዚህ አዋጅ ከተመለከቱ ወንጀሎች ጋር ተያይዘው የሚፈፀሙ ሌሎች ወንጀሎችን፣ ወይም

ሐ) በዚህ አዋጅ መሠረት የቀረበን ክስ ፍርድ ቤቱ የክሱን አንቀጽ የሚቀይራቸውን ጉዳዮች፣

የመዳኘት ሥልጣን ይኖራቸዋል::

፪/ የሀገር መከላከያ ሠራዊት የሀገሪቱን ሉዐላዊነት ለማስከበር በሚያደርገው ውጊያ የተማረከ ሰው የጦር ምርኮኛ መሆን ወይም ያለመሆኑን የመወሰን ሥልጣን በዚህ አዋጅ ለቀዳሚ ወታደራዊ ፍርድ ቤት ተሰጥቷል::

፫/ የዳኝነት ሥልጣንን የተመለከቱ የ፲፱፻፺፯ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ህግ አንቀጽ ፲፫ እና ፲፯(፩)(ለ) ድንጋጌዎች የሽብርተኝነት ወንጀሎችንም ያካትታሉ::

## ክፍል ሰባት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## ፴፪. ለምስክሮች ጥበቃ ስለማድረግ

፩/ ፍርድ ቤት ማንኛውንም የሽብርተኝነት ጉዳይ በሚያይበት ጊዜ በራሱ ተነሳሽነት ወይም በዐቃቤ ህግ ወይም በምስክሩ ጠያቂነት የምስክሩ ህይወት አደጋ ላይ መሆኑን የተረዳ እንደሆነ የምስክሩን ማንነትና አድራሻ በሚስጥር ለመጠበቅ አስፈላጊ እርምጃዎችን ሊወስድ ይችላል:: የሚወስዳቸው እርምጃዎችም በተለይ የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ:-

ሀ) ክሱ የሚሰማበትን ቦታ መወሰን፤

ለ) የምስክሮች ስሞችና አድራሻዎች በፍርድ ቤቱ ትእዛዞች፣ ውሳኔዎችና መዝገቦች ላይ እንዳይገለፁ ማድረግ፤

ሐ) የምስክሮች ማንነትና አድራሻ እንዳይገለጽ ትእዛዞችን መስጠት፤ እና

መ) በፍርድ ቤቱ እየተካሄዱ ያሉ የክስ መስማት ሂደቶች በከፊልም ሆነ በሙሉ እንዳይታተሙ ወይም በማናቸውም መንገድ እንዳይገለፁ መወሰን::

## 31. Jurisdiction over Terrorism Crimes

1/ The Federal High Court and the Federal Supreme Court shall have jurisdiction over:

a) cases presented in accordance with this Proclamation;

b) other crimes committed together with crimes mentioned under this Proclamation; or

c) criminal cases presented in accordance with this Proclamation, which the court changes the article of the charge.

2/ The power to determine the status of a prisoner, captured by the Defense Forces during war conducted to defend the sovereignty of the country, as a prisoner of war or not is hereby given to the Primary Military Court.

3/ Articles 13 and 17(1)(b) of the 2004 Criminal Code of the Federal Democratic Republic of Ethiopia relating to jurisdiction shall also include terrorism offences.

## PART SEVEN
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

## 32. Protection of Witnesses

1/ Where the court, on its own motion or on an application made by the public prosecutor or by the witness, is satisfied that the life of such witness is in danger, it may take the necessary measure to enable the withholding of the name and identity of the witness. The measures it takes may, in particular, include:

a) holding of the proceedings at a place to be decided by the court;

b) avoiding of the mention of the names and addresses of the witnesses in its orders, judgments and in the records of the case;

c) issuing of any directions for securing that the identities and addresses of the witnesses are not disclosed; and

d) ordering that all or any of the proceedings pending before the court shall not be published or disseminated in any manner.

፪/ ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተሰጠን ውሳኔ የተላለፈ እንደሆነ ከአምስት እስከ አሥር ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራትና ከብር ፲ሺ. እስከ ፴ሺ. በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል::

**፴፫. የፍርድ ሂደትን ስለመርዳት**

ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ የተመለከተ ወንጀል በመፈፀሙ በአድራጎቱ የተፀፀተ እንደሆነና ስለወንጀሉ አፈፃፀም በዝርዝር ለማስረዳት የተባበረ እንደሆነ ወይም ወንጀሉን በመፈፀሙ ከርሱ ጋር የተሳተፉ ሰዎችን ያጋለጠ እንደሆነ በዐቃቤ ህግ ጥያቄ መነሻነት ፍርድ ቤቱ ቅጣቱን ሊያቀልለት ይችላል::

**፴፬. ፈንድ ስለማቋቋም**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ መሠረት የሽብርተኝነት ተጎጂዎች ፈንድ ይቋቋማል::

**፴፭. የመተባበር ግዴታን መጣስ**

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፫፣ ፲፬፣ ፲፭፣ ፳፩ ወይም ፳፪ መሠረት የተጠየቀውን ትብብር ያላደረገ፣ ለመተባበር ፈቃደኛ ያልሆነ ወይም በፖሊስ የወንጀል መከላከል ወይም ምርመራ ሥራ ላይ ሆን ብሎ ማናቸውንም እንቅፋት የፈጠረ ማንኛ ውም ሰው ከሦስት እስከ አሥር ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል::

**፴፮. ተፈጻሚ የማይሆኑ ሕጎች**

፩/ ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም::

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እንደተጠበቀ ሆኖ የወንጀል ሕግና የወንጀለኛ መቅጫ ሥነሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ::

**፴፯. ደንብ የማውጣት ስልጣን**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል::

2/ Any person who contravenes any decision or order issued under sub-article (1) of this Article shall be punishable with rigorous imprisonment from five to ten years and with fine from Birr 10,000 to Birr 30,000.

**33. Assisting Judicial Proceedings**

The court may mitigate the punishment, upon a request made by the public prosecutor where the defendant repents about his act of committing any of the crimes mentioned under this Proclamation and cooperates in elaborating in detail the manner of the commission of the crime or discloses the identities of the persons who participated in the commission of the crime.

**34. Establishment of Fund**

Upon the issuance of regulation by the Council of Ministers, terrorism victims fund shall be established.

**35. Breach of Duty to Cooperate**

Whosoever fails or is unwilling to make the requested cooperation, pursuant to Article 13, 14, 15, 21 or 22 of this Proclamation, or intentionally makes any hindrance on the crime prevention or investigation functions of the police is punishable with rigorous imprisonment from three to ten years.

**36. Inapplicable Laws**

1/ No law, regulation, directive or practice shall, in so far as it is inconsistent with this Proclamation, be applicable with respect to matters provided for by this Proclamation.

2/ Without prejudice to the provisions of sub-article (1) of this Article, the provisions of the Criminal Code and Criminal Procedure Code shall be applicable.

**37. Power to Issue Regulations**

The Council of Ministers may issue regulations necessary for the implementation of this Proclamation.

**፴፰. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ነሐሴ ፳፪ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**38. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 28th day of August, 2009**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**